# ብሩህ ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ

# Beruh Ethiopia Democratic Movement

❖

## የሕዝብን ሰላማዊና ህዝባዊ ተቃውሞ ለማፈን ግድያ የፈፀሙ ለፍርድ ይቅረቡ!

## የመሬት ነጠቃና ሕዝብን ከሕዝብ ማጋጨት ይቁም!

የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ የመንግሥት እርካቡን ከረገጠበት የዛሬ ሃያ አምት ዓመት ጀምሮ ሕዝብን ከሕብ፤

ኃይማኖትን ከኃይማኖት ለያይቶና አናክሶ በስልጣን ላይ ለመቆየት የሚያራምደው የፖለቲካ ሂደት ሁለት አደገኛ ሁኔታዎችን

ፈጥሯል። ኢትዮጵያ እንድትፈራርስ፤  በሰላምና በጉርብትና ይኖር የነበረው ሕዝብ በየእርስ በርስ የጎሳና

የኃይማኖት ግጭት ወደ አስከፊ እልቂት እንዲያመራ እያደረገው ነው። ይኽ በአገራችን ያንዣበበ አደጋ ሌላው ቀርቶ ገዢውን ፓርቲም ያጠፋዋል። በእኛ ግምት ለኢትዮጵያ ግዛታዊ አንድነት፤ ሉዐላዊነትና አብሮና ተጎራብቶ በሰላም ሲኖር ለቆየው የኢትዮጵያ 100 ሚሊየን ሕዝብ ፀር የሆነውና አደጋውን የፈጠረው የአምባገነኑ ገዢ ፓርቲ አመራርና የሚከተለው <u>**የከፋፍለህ ግዛው ፖሊሲ**</u> ነው።

ህወሓት በበላይነት የሚቆጣጠረውና የሚያዘው አገዛዝ ባለፉት 25 አመታት በአገር ወዳድነት፤ በጎረቤትነት፤ በአብሮነት ላይበተመሰረተ ማህበራዊ ግንኙነት፤ በጋራ ኢትዮጵያዊ የሆነ ዜግነት፤ አንዱ ከሌላው ጋር ተጋብቶና ተዛምዶ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ነጻነት ያስከበረውንና ለአንድነቱ መስዋእት የከፈለውን ታላቅ ሕዝብ ሆነ ብሎ በጎሳና በኃይማኖት ከፋፍሎት ቆይቷል። ይኼ ሆነ ተብሎ በሕገ መንግሥት የጸደቀና ሲተገበር የቆየ ፖሊሲና አስተዳደር መጠነ ብዙ ጉዳቶችን፤ ግፎችን፤ ግድያዎችን፤ ተከታታይ የሆኑ የወጣት ትውልድ ስደቶችን፤ ረሃብን፤ መጥፎ አስተዳደርን፤ የዘር ማጥፋትን፤ አይን ያወጣ ኪራይ ሰብሳቢነትንና ሌሎችን ሁሉንም ኢትዮጵያዊያን ያደሙና ያደከሙ እርምጃዎችን በተደጋጋሚ ወስዷል።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት፤ ህወሓት/ኢህአዴግ በጋምቤላ፤ በደቡብ ክልል፤ በቤኒ ሻንጉል ጉሙዝ፤ በአማራ፤ በኦሮሚያና በሌሎች ክልሎች ነዋሪውን ሕዝብ ሳያማክር፤ ሳያሳትፍ፤ የተሻለ አማራጭ ሳይሰጥ፤ የነዋሪውን ሕዝብ መሬት እየነጠቀ ለምርጥ የአገር ውስጥና ውጭ ኢንቬስተሮች በገፍ ለግሷል። ብዙ ሚሊየን ሕዝብ ከኑሮው ተፈናቅሏል፤ መብቱ ተገፏል። የንጹህ ኢትዮጵያዊያን ህይወት ወድሟል። በተመሳሳይ፤ በልዩ ልዩ ከተሞች፤ በተለይ የጥቂት የፓርቲና የመንግሥት ባለሥልጣናት ኃብታሞችና ቤተሰቦቻቸው ምሽግ በሆነችው በአዲስ አበባ ዙሪያ ማስተርፕላን የተባለ እቅድ አዘጋጅቶ ከፍተኛ የሕዝብን ንብረት ቀምቷል። ብሩህ፤-- የከተማ መስፋፋት የትም ዓለም የሚካሄድ መሆኑን ሙሉ በሙሉ ያምናል።

ሆኖም፤ የከተማ መስፋፋት በአካባቢው በግብርናና በሌላ ስራዎች የተሰማሩትን ኢትዮጵያዊያን ሁሉ በማሳተፍ፤ በማማከር፤ ጥቅማቸው እንዳይጎዳ በማድረግ፤ ኑሯቸው እንዳይናጋ በማድረግ፤ መሬታቸው ለተነጠቀባቸው ተመጣጣኝ ካሳና አማራጮች በመስጠት የሚደረግ መሆን አለበት። እኛ ይኼን ሕዝብ ያልተሳተፈበትና ያልተመካከረበት ማስተር ፕላን እንደ መጥፎ አገዛዝ እናየዋለን። የመሬት ነጠቃ በተካሄዳባቸው አካባቢዎች ሁሉ፤ አዲስ አበባን ጨምሮ ሕዝብ ያለው አማራጭ ህገ ወጡን ውሳኔ ተቃውሞ ለመብቱ መታገል ብቻ ነው። ገዢው ፓርቲ ያደረገው ለመብታቸው በሰላም ተሰልፈው መብታችን ይከበር የሚሉትን ወገኖቻችን፤ በተለይ ወጣቶቹን እርህራሄ በሌለው ደረጃ የጭካኔ እርምጃ ወስዶባቸዋል። ይኼ ጭካኔ በተከታታይ ያሳየን፤ ገዢውፓርቲ ችግሮችን በሰላም ለመፍታት የማይችል፤ ለመግዛት የሞራል ብቃት የሌለው፤ የመላውን ኢትዮጵያ ሕዝብ እምነት ያጣ፤ በፀረ-ሽብርተኞች አመካኝቶ ራሱ ሽብርተኛ መሆኑን ነው። በአገር ቤትና በውጭ የሚገኙ የሰብአዊ መብቶች ጠበቃ ድርጅቶች፤ የአሜሪካና ሌሎች መንግሥታት፤ የተባበሩት መንግሥታት አካል ተቋሞች ወዘተ ሁኔታው አስጊ ስለሆነ የሕዝብ ጭፍጨፋው እንዲያቆም አሳስበዋል። በብሩህ እምነት፤ በመሳሪያ ኃይል የሕዝብን ቁጣና እምቢተኛነት ለትንሽ ጊዜ ማገብ እንጅ ለማቆም አይቻልም። ምክንያቱም መሰረታዊው የፖሊስ ጥያቄ አይፈታም።

## የሕዝብን ሰላማዊና ህዝባዊ ተቃውሞ ለማፈን ግድያ የፈፀሙ ለፍርድ ይቅረቡ!

## የመሬት ነጠቃና ሕዝብን ከሕዝብ ማጋጨት ይቁም!

አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁለቱም አደጋዎች እንዳይፈፀሙ ይፈልጋል። “እወቁበት፤ ተቻችላችሁ ለችግሮቹ መፍትሄፍ ፈልጉ፤ ትግሉን ብሄራዊ አድርጉት” ይላል። በብሩህ ግምት ሁሉም ተቃዋሚ ፓርቲዎች፤ የማህበረሰብና የሞያ ድርጅቶች፤ መንፈሳዊ አባቶች፤ ሽማግሌዎች፤ ወጣቶችና ኢህአዴግ ደፍረው መወያየት፤ መነጋገርና መደራደር ይገባቸዋል። <u>ብሄራዊ መግባባት</u> ከሌለ አደጋው እየተባባሰ እንጅ እየቀለለ አይሄድም። ብሄራዊ መግባባት ወደ ተፈላጊ ዲሞክራሳዊ ስርዓት ሊወስደን የሚችለው  በኢትዮጵያ የወደፊት እድል የሚያገባቸው፤ በአገር ውስጥና በውጭ የሚገኙ ኃይሎች ሁሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከገዢው ፓርቲ ጋር ለመነጋገርና ለመደራደር ሲችሉ ነው። ብሄራዊ መግባባት ስኬታማ የሚሆነው ግልፅነት፤ ሃላፊነት፤ ደፋርነት፤ ግልፅነት፤ ለአገርና ለመላው ሕዝብ ተቆርቋሪነት ሲኖር ነው። የኢትዮጵያ ዘላቂነት፤ የሕዝብ መብትና የሕዝብ ጥቅም መአከል መሆን አለባቸው።  ብሄራዊ መግባባት በአስቸኳይ ከተካሄደ ሌሎችን ችግሮች ለመፍታት የሚቻልበት ሁኔታ ይመቻቻል የሚል እምነት አለን።

ህወሓት/ኢህአዴግ በማስተር ፕላን፤ በእድገት፤ በእርጋታ፤ በጸረ-ሽብርተኛነትና በሰላም ወዘተ ስም ለራሱ የስልጣን ቆይታ፤ ለራሱ ቡድን የገንዘብና የተፈጥሮ ኃብት ጥቅም የሚያደርገውን የመሬት ነጠቃና የህዝብ መብቶች አፈና እንቃወማለን፤ ግድያዎቹን እናወግዛለን። ድርጅታችን ብሩህ፤ የተቀነባበረ የሕዝብ አመጽ አግባብ እንዳለው ያምናል። ሕዝባዊ አመጽ ስኬታማ ሊሆን የሚችለው በመተባበር ብቻ ነው። ብሩህ ለኢትዮጵያ ብሄራዊ አንድነት፤ ሉዐላዊነትና ለመላው ሕዝቧ ነጻነት፤ ለሰብአዊ መብቶች መከበርና፤ በዘላቂነት ደረጃ ሁሉንም ኢትዮጵያዊያን ለሚያስተናግድ ዲሞክራሳዊ አገዛዝ አማራጭ የሚታገል መሆኑን እንደ ገና ይገለጻል።

ብሩህ የተለያዩ የትግል ስልቶችእንዳሉ ያውቃል። እንቅስቃሴያችን በሰላማዊ ትግልና በሕዝብ ዐመጽ እምነት ቢኖረውም፤ <u>ብሄራዊ የሆነ የዓላማ አንድነት ይዘው በአንድነት እስከተነሱ</u> ድረስ ሁሉም ተቃዋሚ ክፍሎች አብረው፤ ተባብረው፤ ተፈላልገው፤ ተናብበውና አንድነት ፈጥረው አፋኙንና አምባገነኑን አገዛዝ ለመጣል አሁንም እድል አላቸው ይላል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ምኞትና ፍላጎት ራሱ የፖለቲካ ስልጣን ባለቤትና የልማት መአከል መሆኑን ነው። ለሁሉም የሚበቃ እምቅ የተፈጥሮና የሰው ኃብት ባለቤት የሆነችው አገራችን አሳታፊ፤ ሕዝብን የፖለቲካና የኢኮኖሚ እድገት መአከል ያደረገ አገዛዝና አመራር ከመሰረተች ዘላቂነትና ፍትሃዊነት ያለው እድገት መሰረት እንደምትጥል ሙሉ እምነት አለን።

ብሩህ ለተቃዋሚ የፖለቲካ፤ የማህበረስብና የሞያ ድርጅቶች፤ ታዋቂ ግለሰቦች፤ የኃይማኖት መሪዎች፤ አባቶች፤ እናቶችና ወጣቶች የሚያቀርበው አስቸኳይ ጥሪ ጥቃቅን ልዩነቶችን ወደጎን በመተው፤ በመቻቻል፤ በመከባበር፤ ችግሮችን በድፍረት አብረን ለመፍታት በመወሰን፤ አገር አቀፍ የሆነ፤ የተቀነባበረ ሕዝባዊ ትግል ስር እንዲሰድና ፈር እንዳይለቅ በማድረግ አምባገነኑን ስርዓት አስወግደን እውነተኛ ዲሞክራሳዊ ስርዓት እንዲመሰረት ቆርጠን እንነሳ የሚል ነው። ይቻላል!

## ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

## የኢትዮጵያ ሕዝብ በጎሳና በኃይማኖት አይለያይም!

## ፍትህ በአንድነት!

Beruh@Ethiopia.org